# አብይን ተዋጉ!

በግሯ ትሄዳለች ፣ እንቁላል ፣ ቀስ በቀስ
የተለፈለፈው ፣ መስሏቸው የማይደርስ
አገር ገንቢ ፣ ያልነው ፣ ትላንትና ሲነግስ
ካለ ልኩ ፣ ቀደን ፣ ማንነት ሲላበስ
ዓመት ሳያስቆጥር ፣ አየን ፣ አገር ሲያፈርስ ፣
እባቡ ፣ እንደ ርግብ ፣ ሲሞካሽ ሲወደስ
የታመነው ፈረስ ፣ ጥሎናል በደንደስ
አላባራ ብሏል ፣ ደሃውን ማስለቀስ
አቢቹ ፣ እስስት ነው ፣ እንደ ሚቹ ፣ መለስ ።

ያስተሳሰብ ደሃ ፣ ዘውጉ ሃይማኖቱ
ኢትዮጵያን ደመኛ ፣ አርገው የተፋቱ
ከጎሳው ያልመጣ ፣ ሰው ሁሉ ጠላቱ
አሻግሮ የማያይ ፣ ካልሆነ የዕለቱ
የእውቀት መፃጉ ፣ ተልባ ቢከፈቱ
ጥላቻ ነግሶበት ፣ ጠፍቶት ማንነቱ
ታሪክ ተመርኩዘው ፣ ተሟግተው አይረቱ
ነገ ፣ እርስ በርሳቸው ፣ ለሚፈታፈቱ
አገርና ዜጋን ፣ ያደከማሉ ከንቱ ።

በማንነታቸው ፣ የሚሽማቀቁ
ከህሊናቸው ጋር ፣ የማይታረቁ
ሃራምባና ቆቦ ፣ የሚዘባርቁ
እንኳን ሳይማሩ ፣ ተምረው አይነቁ
ሰውን በሰውነት ፣ ጭራሽ የማያውቁ
ማፈራረስ እንጂ ፣ መገንባት አያውቁ
በጦር ተደራጅተው ፣ አንዴ ከታጠቁ
እንኳንስ ለቅርቡ ፣ ያሰጋል ለሩቁ
ይበጃል በጊዜ ፣ አውቆ መጠንቀቁ ።

ኦዴፓ በል ፣ ኦነግ ፣ የቁቤ ተማሪ
የተምታታባቸው ፣ ብኩን ቀባጣሪ
ከሰው የማይገጥም ፣ የእንሰሳ ባህሪ
ብቃት ችሎታቸው ፣ ካልሆነ አጋፋሪ
አይመጥኑም ጭራሽ ፣ መሆን አገር መሪ
አያሻንም መሆን ፣ ትንቢት ተናጋሪ
ባይን የሚታየውን ፣ መርዶ ለቀባሪ
ገና ከጅምሩ ፣ ስራቸው መስካሪ ።

ህዝብ የሰጣቸውን ፣ ክብርና ማዕረጉ
አላውቅበት ብለው ፣ ጭራሽ ያለወጉ
በዘውጌ ፣ ባገር ልጅ ፣ እየሰገሰጉ
ኢትዮጵያዊነትን ፣ እያጠወለጉ
ጭምልቅልቅ ስላለ ፣ በየጥጋጥጉ
አይናችሁ ያየውን ፣ ሃቁን ሳትሸሽጉ
ለአብይ እና ፣ ለማ ፣ ይብቃ ማደግደጉ
የጫጉላ ጊዜያቸው ፣ ተፈትኗል ሰርጉ
የመርዝ ብልቃጦች ፣ ይውጡ ይጠረጉ
የሳር እባቡንም ፣ አብይን ተዋጉ ።

ታዛቢው

March 5, 2019